# ግንቦት ሰባት - ጉዳዩ ኢትዮጵያዊነት ነዉ


## ግርማ ካሳ

(muziky68@yahoo.com)


---

ትዝ ይለኛል በጥቅምት ወር 1984 ዓ.ም አካባቢ ነበር ሁለት ጓደኛምች በቸርችል ጎዳና፣ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጀርባ በሚገኘዉ የ"ትግላችን" ሃዉልት ጋር ፎቶግራፍ ለመነሳት የቆሙት። (ይህ ሃዉልት አሁን ይኖር አይኑር አላዉቅም) እነዚህ ወጣቶች፣ የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማሪያም ምስል የሚታይበትን ሃዉልት አክብረዉ ሳይሆን እዚያ ቦታ ፎቶግራፍ ለመነሳት የቆሙት፣ ከሃዉልቱ በስተግራ በኩል መሬቱ ላይ ተተክለዉ የነበሩ አበባዎች ማርከዋቸዉ ስለነበር ነዉ።

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ አበባዎች መስመሩን በጠበቀ መልኩ ተተክለዉ የኢትዮጵያ ባንዲራ መሬቱ ላይ የተዘረጋ አስመስለዉት ነበር።

በወቅቱ ኢትዮጵያዉነት እንደ ወንጀል፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ ደግም እንደ ተራ ጨርቅ የሚቆጠርበት አሳዛኝ ወቅት ስለነበረ "ኢትዮጵያዊነታችንን የሚወስድብን ማንም የለም" ሲሉ ነበር ወጣቶቹ በወቅቱ ለነበረዉና አሁንም ላለዉ የነአቶ መለስ/ስብሃት/በረከት አገዛዝ ተቃዉሞዋቸዉን የገለጹት። ጉዳዩ ከትግላችን ሃዉልት ወይንም ከአበባዎቹ ሳይሆን **ጉዳዩ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ነበር።**

ትዝ ይለኛል መስከረም 1 1984 ዓ.ም፣ የአበሻ ልብስ ለብሰዉ፣ አሁንም በቸርቸል ጎዳና ከፒያሳ ወደ ለገሃር ሲራመዱ የነበሩ አምስት ወጣት ወንዶች። መኪና ነጆዎች የመኪናቸዉን ክላክስ እየነፉና በመስኮት እጃቸዉን እያዉለበለቡ፣ እግረኞች ደግም ሰላምታ እየሰጡ ለነዚህ አምስት ወጣቶች አክብሮታቸዉን አድናቆታቸዉን ይገለጹ ነበር።

ጉዳዩ ከወጣቶቹ ወይንም ከለበሱት የአበሻ ልብስ አልነበረም። ጉዳዩ ወጣቶቹ በለበሱት የአበሻ ልብስ የአንገትና የእጅ ዘርፍ ዙሪያ ተሰፍተዉ በነበረዉ፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለማት ባላቸዉ ጨርቆች ነበር። **ጉዳዩ በወቅቱ ጥቃት ይደርስበት ከነበረዉ ከ"ኢትዮጵያዊነት" ጋር ነበር።**

ግንቦት ሰባት 1997 ዓ.ም በተደረገዉ ምርጫ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ ታይቶ የማይታወቅ አስደናቂ ተዓምር ማሳየቱ ይታወሳል። እነ አቶ መለስ ዜናዊ ሥልጣን ከጨበጡ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያዊነትን ሲያጥላሉ፣ ዜጎች ለኢትዮጵያዊነት ሳይሆን ለጎጣቸዉ ቅድሚይ እንዲሰጡ ሲያደርጉ፣ ኢትዮጵያን እንደ አንዲት ሉዓላዊ አገር ሳይሆን እንደ ተራ እቃ ሲቆጥሯትና ሲቆራርጧት አመታት አሳልፈዋል።

ታዲያ በግንቦት ሰባት 1997 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኘዉን ትንሽ ቀዳዳ በመጠቀም ነበር በማያዳግም ሁኔታ እቅጭ ቅልብጭ ያለዉን ድምጹን የሰጠዉ። ለአመታት ሲያደነቁረዉ የነበረዉን የዘር ፖለቲካ "እጸየፈዋለሁ" ነዉ ያለዉ። በመቱ፣ በጎሬ፣ በአምቦ፣ በድሬደዋ፣ በጎንደር፣ በጅጅጋ፣ በደብረ ብርሃን፣ በጎባ፣ በደሴ፣ በአዋሳ ...በየክልሎቹ በገጠርና በከተማ ኢትዮጵያዊነትን ነበር የመረጠዉ።

በምርጫ ዘመና ሰባት ሕብረትና ቅንጅት በጋራ አሸናፊ እንደሆኑ ቢታወቅም ጉዳዩ ከቅንጅትም ሆነ ከሕብረት መሪዎች ጋር አልነበረም። **ጉዳዩ ከ"ኢትዮጵያዊነት" ጋር ነበር።**

የግንቦት ሰባቱ ቀን በጎላ መልኩ የሚያስታወሰን የኢሕአዴግን መሸነፍ ወይንም የቅንጅትና ህብረት ማሸነፍ ሳይሆን የኢትዮጵያዊነት ማሸነፍን ነዉ። ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ቦታ የማይሰጥ፣ ኢትዮጵያዉያንን በዘርና በኃይማኖት የሚከፋፍልና ኃላ ቀር የሆነ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ቦታ እንዳማይኖረዉ ነዉ በማያሻማ ሁኔታ ግንቦት ሰባት ያሳየዉ።

መርሳት የሌለብን አንገብጋቢ ቁምነገር አለ። ግንቦት ሰባት የጉዞዉ መጨረሻ አይደለም። ተሰፋይቱ ምድር ገና አልደረስንም። ነጻነ የአገሬ ልጅ፣ ፍርሃትንና ተስፋ መቁረጥን ከላያችን ላይ አዉለቀን "ይቻላል" በሚል ቁርጠኝነት አገራችንን ከመፈረካከስ፣ ከድህነት ከበሽታና ከጦርነት እናድን።

## እኛ ካልተነሳን ማን ?
## አሁን ካልተነሳን መቼ ?